እነዚህ ድንጋጌዎች በሲያትል ከተማ ክልል ውስጥ የሚሰሩትን ሰራተኞች በሙሉ ያጠቃልላሉ፣ የኢሚግሬሽን ሁኔታን ወይም የአሰሪያቸውን አድራሻ ሳይመለከት።

# 2016 የሲያትል የሰራተኛ መመዘኛ ድንጋጌዎች (Seattle Labor Standards Ordinances)

የ Office of Labor Standards ተልእኮ፣ ለዘርና ለማህበራዊ ፍትህ ታጥቆ በመነሳት፣ በቅን ልቦና ከማህበረሰብና ከንግድ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በማድረግ፣ ስልታዊ በሆነ መንገድ ሕግን በማስከበርና በአዲስ ዘዴ መመሪያዎችን (ፖሊሲዎችን) በማዘጋጀት የሰራተኛ መመዘኛዎችን ከፍ ማድረግ ነው።

ይህ ማስታወቂያ ጽሁፍ (ፖስተር) በደንብ ሊታይና ሊደረስበት በሚችል የስራ ቦታ ላይ በእንግሊዘኛና በሰራተኞቹ ቋንቋ(ዎች) ተጽፎ መለጠፍ አለበት።

SMC 14.19

## መነሻ የደሞዝ መጠን

**ለሰራተኞች መነሻውን የደሞዝ መጠን ይመድባል**

### ትላልቅ አሰሪዎች
(501 ወይም ከዚያ የበለጡ ሰራተኞች)

አሰሪው ለግለሰብ ሰራተኞች የህክምና ጥቅሞች የሚከፍለው ገንዘብ አለ?

| አይ | አዎ |
|---|---|
| **$13.00** በሰዓት | **$12.50** በሰዓት |

### ትናንሽ አሰሪዎች
(500 ወይም ከዚያ ያነሱ ሰራተኞች)

አሰሪው ቢያንስ **$1.50** በሰዓት ለሰራተኛው የህክምና ጥቅሞች ይከፍላል እና/ወይም ሰራተኛው ቢያንስ **$1.50** በሰዓት ቲፕ ያገኛል?

| አይ | አዎ |
|---|---|
| **$12.00** በሰዓት | **$10.50** በሰዓት |

**የአሰሪ መስሪያ ቤት ትልቅነት**

አሰሪው በዓለም አቀፍ ያሉትን ጠቅላላ የሰራተኞች ቁጥር ይቁጠሩ። ለባለፍራንቻይዚ አሰሪ፣ በፍራንቻይዚ ውስጥ ያሉትን ሰራተኞች ሁሉ ይቁጠሩ።

**የህክምና ጥቅሞች**

በ Federal Affordable Care Act በተገለጸው መሰረት ሰራተኞች በብር-ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ በተመደበ የጤና መድን እቅድ (ኢንሹራንስ ፕላን) ውስጥ መመዝገብ አለባቸው።

» ሰራተኛው የህክምና ጥቅሞችን አልፈልግም ካለ ወይም ለህክምና ጥቅሞች ብቁ ካልሆነ፣ አሰሪው የተቀነሰ መነሻ የደሞዝ መጠን ሊከፍለው አይችልም።

SMC 14.20

## የደሞዝ ስርቆት

**ከደሞዝ ስርቆት ይከላከላል**

**አሰሪዎች በአንድ መደበኛ የስራ ቀን ላይ መከፈል ያለበትን የካሳ ክፍያ ሁሉ መክፈልና ለሰራተኞቹም ስለ ስራቸውና ክፍያቸው በጽሁፍ መረጃ መስጠት አለባቸው።**

**በጽሁፍ የተዘጋጀ መረጃ የሚከተሉትን ማጠቃለል አለበት፥**

- የአሰሪውን ስምና የመገናኛ (ስልክ) መረጃ።
- አሰሪው የሚከፍለው የክፍያ ደረጃ፣ ለኦቨርታይም ክፍያ ብቁነት፣ የሚከፈለው (በሰዓት፣ በፈረቃ (ሽፍት)፣ በቀን፣ በሳምንት፣ ኮሚሽን)፣ እና መደበኛ የክፍያ ቀን።
- ስለ አሰሪው የቲፕ መመሪያ ማብራሪያ።
- በክፍያ ቀኖች ላይ ስለሚሰጠው ክፍያ የተዘጋጀ ዝርዝር መግለጫ።

**የክፍያ ማሟያ ነጥብ ምሳሌዎች፥**

- መነሻ የደሞዝ መጠን ይከፍላል።
- ኦቨርታይም ይከፍላል።
- የስራ እረፍት ጊዜዎችን ይሰጣል።
- እከፍላለሁ ብሎ ቃል የገባውን መጠን ይከፍላል።
- ከስራ ሰዓት ውጭ ለተሰራ ሥራ ይከፍላል።
- የተገኙ ቲፖችን ይከፍላል።
- ለአሰሪ ወጪዎች መተኪያ ይከፍላል።
- ሰራተኞችን በትክክል በመደባቸው ይመድባል፤ እንደ የግል ተኮናታሪ ሰራተኛ አድርጎ ያለመደባቸው አይመድቡም።

SMC 14.17

## ለስራ ቅጥር ፍትሃዊ እድል

**የወንጀል ፍርድና የእስራት መዝገቦችን ለመጠቀም ገደብ ያደርጋል**

**የተከለከሉ ነገሮች፥**

- በወንጀል የተፈረደባቸውንና የእስራት መዝገብ ያለባቸውን አመልካቾች የሚያገሉ የስራ ማስታወቂያዎች።
- ስለ ወንጀል ፍርድ ወይም የእስራት መዝገብ ጥያቄ ያላቸው የስራ ማመልከቻዎች፣ አሰሪው ለአመልካቾቹ በቅድሚያ ለቀላል የብቁነት መስፈርቶች ማጣሪያ አድርጎ ከነበረ እንጂ።
- በእስራት መዝገብ ምክንያት ብቻ ስራ መከልከል (ወይም ሌሎች የከፉ በስራ ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች)።

**አንዳንድ የሚደረጉ ልዩ አስተያየቶች አሉ፣ እነሱም እድሜያቸው ከ 16 በታች ለሆኑ ልጆች ቁጥጥር የማይደረግበት፣ በአካል እድገት ለታጎሉ ሰዎች፣ ወይም ለአደጋ ለተጋለጡ ጎልማሳዎች አገልግሎት የሚያቀርቡ ስራዎችን ይጨምራሉ።**

**አሰሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርባቸዋል፥**

ለአመልካቾች ቀላል የብቁነት መስፈርቶች ማጣሪያ እስከሚደረግ ድረስ የወንጀል ታሪክ ማጣሪያን ማዘግየት።

የወንጀል ታሪክ ማጣሪያን ብቻ ተመርኩዞ የከፋ እርምጃ ከመውሰድ በፊት መመሪያ ደንቦችን መከተል፥

» ስለ ወንጀል ታሪክ ማጣሪያ መረጃ ማብራሪያ እንዲሰጥ ወይም እንዲስተካከል እድል መስጠት።

» የስራ ቦታውን ቢያንስ ለሁለት የስራ ቀኖች ክፍት አድርጎ መጠበቅ።

» ይህንን ግለሰብ መቅጠር ስራውን እንደሚጎዳ ወይም ሰራተኛው ስራውን ለመስራት ያለውን አቅም እንደሚያውክ ተገቢ ስራ ነክ ምክንያት ይኑርዎ።

SMC 14.16

## ለህመምና ለደህንነት ጊዜ ክፍያ

**ለህክምና ወይም ለደህንነት ጉዳዮች ተከፍሎ የእረፍት ግዜ እንዲኖር ያዛል።**

**ሰራተኞች ለእራሳቸው ወይም ለቤተሰብ አባላቸው እንክባክቤ ማድረግ እንዲችሉ አሰሪዎች ደሞዝ የሚከፈልበት የእረፍት ግዜ ለሰራተኞች መስጠት አለባቸው።**

**የህመም ጊዜ፥** የአካል ወይም የአእምሮ ጤና ሁኔታ፣ ለህክምና ቀጠሮንም ጨምሮ።

**የደህንነት ጊዜ፥** ከቤተሰብ ብጥብጥ፣ ከግበረ ስጋዊ ጥቃት፣ አድብቶ ከመከታተል ወይም ከሌሎች የሕዝብ ደህንነት ጉዳዮች ጋር የሚገናኙ ምክንያቶች።*

**ለህመምና ለደህንነት ጊዜ ክፍያ (PSST) የክፍያ ደረጃዎች**

| | ምድብ 1 | ምድብ 2 | ምድብ 3 |
|---|---|---|---|
| **የአሰሪ መስሪያ ቤት ትልቅነት** ዓለም አቀፍ ከሙሉ የስራ ሰዓት ጋራ የሚስተካከል የሰራተኞች ብዛት (FTES) | ከ 4 በላይና እስከ 49 FTEs | 50 – 249 FTEs | 250+ FTEs |
| **የ PSST ጥርቅም** ለእያንዳንዱ ስራ የተሰራበት ሰዓት | 1 ሰዓት በ 40 ሰዓታት ውስጥ | 1 ሰዓት በ 40 ሰዓታት ውስጥ | 1 ሰዓት በ 30 ሰዓታት ውስጥ |
| **ያልተጠቀሙባቸውን የ PSST ሰዓታትን አጠቃቀምና ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ** በአንድ የጥቅም ዓመት ውስጥ | 40 ሰዓታት | 56 ሰዓታት | 72 ሰዓታት** |

*የደህንነት ጊዜ እቤትዎ ውስጥ የሚኖር ባልንጀራዎን ለመንከባከብ ሊያገለግል ይችላል

**108 ሰዓታት እየተከፈለ የሚሰጥ የእረፍት ቀን (PTO) ፖሊሲ ላላቸው የምድብ 3 አሰሪዎች

**አሰሪዎች እነዚህን ሕጎች መከተል አለባቸው። የቂም በቀል እርምጃ ሕገ-ወጥ ነው።**

የሕግ ጥሰቶችን ያሳውቁ

ለ Office of Labor Standards አቤቱታዎን ያቅርቡ

*-ወይም-* በሚከተለው* ቀን ላይ ወይም ከዚያ በኋላ በፍርድ ቤት ክስ ይመስርቱ፥

- ሚያዚያ (አፕሪል) 1, 2016፣ 50 ወይም ከዚያ በላይ ሰራተኞች ላሏቸው አሰሪዎች
- ሚያዚያ (አፕሪል) 1, 2017፣ ከ 50 ያነሱ ሰራተኞች ላሏቸው አሰሪዎች

*በፍርድ ቤት ክስ ሊቀርብ የሚችለው የመነሻ ደሞዝ መጠን፣ የደሞዝ ስርቆት፣ እና የህመምና የደህንነት ጊዜ ክፍያ ሕግ በሚጣስ ጊዜ ብቻ ነው።

**በሚስጥር የሚያዙና በነጻ የሚሰጡ አገልግሎቶች**

- የአቤቱታ ምርመራዎች።
- ለሰራተኞች ቅስቀሳ።
- ለንግድ ድርጅቶች የቴክኒክ እርዳታ።
- መርጃ ምንጮችና መምሪያዎች።

ለቋንቋ የቃል፣ የጽሁፍ ትርጉም አገልግሎቶችና መስተንግዶዎች ይኖራሉ።

**(206) 684-4500**

seattle.gov/laborstandards

**OFFICE OF LABOR STANDARDS** 810 THIRD AVE, STE 750, SEATTLE, WA 98104 (206) 684-4500 LABORSTANDARDS@SEATTLE.GOV ሰዓታት፥ 8 ጠዋት–5 ከሰዓት (ከሰኞ-ዓርብ)

ታተመ፥ 04/04/16